## המשך פעילויות בעקבות הסיפור - ሙዚቃ




በ: ዲቦራ ቡሼሪ
ምሳሌዎች: ኖአ ኬልነር
הוֹצָאָה: הוצאת כנרת
የእድሜ ክልል: ታዳጊዎች

כְּלָלִי

**ለቤተሰባዊ ንባብ ጠቃሚ ምክር**

ታዳጊ ሕጻናት የታሪኩ አካል መሆንን ይወዳሉ፡- በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ቃላትና ድምጾች መድገም ወይም የመጽሐፉን ጀግኖች ድርጊት መተወን። በዚህ መንገድ ታሪኩን ይለያሉ፣ ስሜታዊ የሆነው ዓለማቸውን ያበለጽጋሉ፤ ቃላትንና ጽንሰ-ሐሳቦቻቸውን ያገኛሉ። ስለዚህ የጋራ ንባብ ላይ ጥሩምባን ይዞ "መንፋት"፣ ከበሮውን በእጆቻችሁ "መምታት" እና የሕብረት መዝሙሮች ላይ "መምራት" ይገባል።

כְּלָלִי

**ውይይት**

ጊሊ ለእርሷ የሚስማማ ሚና አግንታ ኦርኬስትራውን ትመራለች። እርሱን ተከትሎ በቤት ውስጥ ስለ ታዳጊ ሕጻናት ሚናዎች መወያየት ይችላሉ- ምን ያውቃሉና ምን ማድረግ ይፈልጋሉ – መጫወቻዎችን መሰብሰብ? ወለል መጥረግ? ?ለምግብ ጠረጴዛ ለማዘጋጀት መርዳት

כְּלָלִי

**ታሪኩን ማዳመጥ**

**ኦርኬስትራው በጊሊ መሪነት እንዴት ይሰማል? – ኮዱን ስካን ያድርጉና ታሪኩን ያዳምጡ።**

כְּלָלִי

**አብሮ መጫዎት**

**ማንኛውም ነገር ማለት ይቻላል የሙዚቃ መሳሪያ ሊሆን ይችላል፡- ወደ ዘፈኑ ዜማ እጆቻችሁን በአንድ ላይ ማጨብጨብ ወይም ያገኙትን የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ማራካሾችና መሳሪያዎች መሰብሰብ ይችላሉ። ማንኪያ ያለው ድስት ከበሮ ሊሆን ይችላል፤ ጥቅል ወረቀት እንደ ጥሩምባ ሊያገለግል ይችላል። እንዲሁም የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመምታት መሞከርና መፈተን ይችላሉ፡- በእንጨት ሲመታ ምን ዓይነት ድምፆችን ያወጣል? በወለል ንጣፍ ላይስ? በብረት ላይስ? የሚወዱት ዘፈን ላይ ይወስኑና አንድ ላይ መጫወት ይችላሉ።**

כְּלָלִי

**ኦርኬስትራን መምራት**

**ማን ነው የሚመራው ማን ነች የምትመራው? – የሚወዱትን ሙዚቃ አንድ ላይ ሲያዳምጡ ትንሽ ዱላ በመያዝ ተጫዋቾቹን "መምራት" ይችላሉ። የሙዚቃው ድምጾች ላይ መደነስና የተለያዩ መሳሪያዎች ላይ መተወን፤ አልፎ አልፎም ሚናዎችን መቀያየር ይችላሉ።**

הַשְׁרָאָה

[**የፈጠራ ስራዎችን፣ ዘፈኖችንና ሌሎችን ስራዎች በፒጃማ ቤተ-መጽሐፍት ፒንተረስት ላይ**]

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org